ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

# የኤም ፖክስ (Mpox) በሽታ ወቅታዊ ማብራሪያ
# ሐምሌ 02 /2017 ዓ.ም

በሀገራችን የመጀመሪያው የኤምፖክስ ታማሚ ከተገኘበት ከግንቦት 16/ 2017 ዓ/ም እስከ ዛሬ ሐምሌ 02 ቀን 2017 ዓ/ም ድረስ በአጠቃላይ ለ520 በበሽታው ለተጠረጠሩ ሰዎች የላቦራቶሪ ምርመራ የተደረገ ሲሆን ከተመረመሩት መሃል 26ቱ በበሽታው እንደተያዙ ተረጋግጧል። ከእነዚህ ታማሚዎች መሃል የአንድ ታማሚ ህይወት ያለፈ ሲሆን የተቀሩት 25ቱ ታማሚዎች ህክምናቸውን በአግባቡ ተከታትለው ሙሉ በሙሉ ከበሽታው አገግመው ወጥተዋል።

በአሁኑ ወቅት በለይቶ ማከሚያ ማእከላት ወስጥ ህክምና ላይ የሚገኝ ታማሚ ባይኖርም፣ አሁንም ወረርሽኙን በአጭር ጊዜ ለመቆጣጠር እና የህብረተሰባችንን ጤና ለመጠበቅ የጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከክልል የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች እንዲሁም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በየደረጃው በተቋቋሙ የድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከላት አማካኝነት የኤምፖክስ በሽታ ቅኝትና ምላሽ ስራዎችን በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ በትኩረት መስራቱን ይቀጥላል፡፡

በዚህም መሰረት፣ በአሁኑ ሰአት ካለው የታማሚዎች ቁጥር እና ፍሰት አንጻር በየቀኑ ለህብረተሰቡ እንስጥ የነበረውን የበሽታው ወቅታዊ መረጃ እንደአስፈላጊነቱ በየሳምንቱ መስጠት የምንቀጥል መሆኑን እያሳወቅን ህብረተሰባችንም ለበሽታው አጋላጭ ከሆኑ መንገዶች በመጠንቀቅ እና የመከላከያ መንገዶችን ችላ ሳይል በመተግበር የበሽታውን ስርጭት በዘላቂነት እንድንገታ በድጋሚ አሳስባለሁ።

**ዶ/ር መቅደስ ዳባ**

**የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**ሐምሌ 02 /2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**